# “ጅብ ከማያውቁት አገር ሂዶ…”

*የጋሻ ለኢትዮጵያውያን መግለጫ*

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ሃገራችን የጦርነት አደጋ ተጋርጦባት ይገኛል። ከኤርትራ ጋር የተደረገው ዘግናኝ ጦርነት ከሰባ ሺ በላይ ወጥቶችን ህይወት በቀጥፍና፣ የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት ቢያሟጥጥም ለአቶ መለስ ዜናዊ ግን የጠላት ኃይልና ንብረት ነበረና ጦርነቱን ኢትዮጵያን በሚቀጣ መልኩ አሰናክሎ አስቀርቶታል።

ለአስራ አምስት አመታት የኢትዮጵያን ስልጣን ተቆጣጥሮ የሚገኘው ይህ ደምኛ ጠላት ዛሬ ደግሞ ጅብ ከማያውቁት አገር ሂዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ እንደሚባለው የአበው ምሳሌ የኢትዮጵያ ህልውና የሚፈታተን ጠላት ተነስቷል፡፡ እና ዝመት! ክተት! በማለት ቡራ ከረዩ ሲል ይታያል። ሃቁ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ በገጠመው ሰር-የሰደደ ተቃዎሞ ለመቀልበስና ብሎም ግዜ ገዝቶ ህዝቡ ለዲምክራሲያዊ ስርዓት የሚያደርገውን ትግል በማዳከምና በመጨፍለቅ የስልጣንን ዘመኑን ለማራዘም ነው። ምንም እንኳ አክራሪ የእስልምና ኃይሎች ለኢትዮጵያ በጎ ይመኛሉ የሚል እምነት ባይኖረንም፣ ድንበር ጥሰው አገራችንን እስካልወረሩ ድረስ ግን ኢትዮጵያን ወስዶ ወደ እሳት መማገዱ መለስ ዜናዊን እንጂ ማንንም የሚጠቅም እንዳልሆነ ግልፅ መሆን አለበት።

የአሁን ወደ ሶማልያ ዘው ብሎ መግባት በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ በተደጋጋሚ የቦንቦች ፍንዳታ አደጋ ሲያደርሱ አንዲት አዛውንት ተናገሩት የተባለውን አስተያየት እንድናስታውስ ያደርገናል። “ለመሆኑ እነዚህ ሁሉ ቦንቦች የሚያፈነዳው ማን ይሆን ብለው ይጠረጥራሉ?” ብሎ አንድ ጋዜጠኛ አዛውንትዋን ሲጥይቅ፣ "ሌላ ማን ይሆናል! ጭር ሲል የማይወዱት እነ አጅሬዎቹ ይሆናሉ እንጂ" በማለት ይመልሱለታል፡፡

ለዲሞክራሲያዊ ስርኣት ተዘጋጅተናል ብለው ምለው በገቡበት ምርጫ ጉድ ሲሆኑ ለስርኣት-ዲሞክራሲ የተዘጋጀውን የሃገሩ ህዝብ የገደሉትን ገድለው፤ ወደ ተለያየ የማሰቃያ ስፍራ ያጋዙትን ካጋዙ በሃላ የዚሁ ዓለም ያስገረመውን መጠነ ሰፊ ግፋቸው አቅጣጫ ለማረሳሳት አንዴ በአክራሪ ሞስሌሞች ሌላ ጊዜ በተገንጣይ ሻዕብያና ኦነግ ሌላም ጊዜ በሽብርተኞች ሃገሪቱ እንደተከበበች በማቅረብ አሁንም ቢሆን ህዝቡ በእነሱ የመሪነት አገዛዝ እንዲተም ለማድረግ ሌት ተቀን ሲደክሙ ይታያል። ለሰላሳ አመት ያሞኙበትን ዘዴ አሁንም ከመከለሱ የተሻለ ሌላ አማራጭ አጥቷል። ለነገሩ እንዲህ አይነት ማስፈራርያ በአመሪካው የሪፓብሊካን መሪዎችንም ለተወሰነ ጊዜ ጠቅሟል።

እኛ ከነጩ ቤተ-መንግስት ከወጣን ልባችሁን ሞልታችሁ ኣትተኙም፤ ዴሞክራቶች እንደሆኑ ኣገርን መጠበቅንና መከላከልን ኣያውቁበትም፤ ለሽብርተኞች በራችንን በመክፈት ኣሳልፈው ይሰጡናል የሚለውን ልብ-ኣድርቅ ክርክር ለተወሰነ ጊዜ ሰርቶላችዋል። ይሁን እንጂ ኣመሪካውያን ስልቱን ለማወቅ ብዙም ኣልወሰደባቸውም። ባለፈው የምርጫ ውጤትም የታየው ቢኖር ይሀው ነው። ከወቅታዊ ቀውስ ለማገገም ሌላ ቀወስን ከሰማይ ከመለመን ሌላ ህወሓቶች መልካም የማይመኙ ለመሆናቸው በመጀመሪያ በትግራይ ሕዝብ ከዚያም በመላ ኢትዮጵያውያንና በዓለም ህብረተ-ሰብ ጋሃድ ከሆነ ቆይቷል። ከበፊቶቹ ሁለት ምርጫዎች የጉንበት 97 በተሻለ መንገድ እንዲሆን የተገደዱበትም ሁለት ዋና ምክንያቶች ነበሩ ማለት ይቻላል። ኣነደኛው የምዕራባውያን ግፊት ሲሆን ሌላው ደግሞ እ.ኣ.ኣ. በ2001 ካአመራር ካገለልዋቸው የተሻሉ ሆነው በመቅረብ በተለይም ከትግራይ ውጭ ባለው ሌላ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ድጋፍ በማሰባሰብ በድርጅታቸው የተከሰተውን ውጥረት ለማርገብ ለመኖሩ ከምርጫው ውጤት በሃላ ሁሉም የተገነዘበው ሃቅ ሆኗል።

ይህ ሁሉ ለማተት የተገደድነው የህወሓት ጉድ የማይታወቅ ሆኖ ሌላውን ለማሳወቅ ሳይሆን፤ በጥቂቱም ድርጊቶቻቸውን በማስታወስ ለወደፊቱ በሚደረጉት ጉዳዮችና የውሳኔ ኣሰጣጥ መንገዶች ለሚኖረን ግምት ይረዱ ይሆናል ከሚል ነው። ይሀውም እስከኣሁን የጠቀስናቸው የሀወሓት/ኢህኣዴግ ባህሪያት በምንም ኣይነት መልክና መመዘኛ የማያቀራርቡ፤ ኣብረው የማያሰሩ በመሆናቸው እንድያውም ኣርቆ ከማሰብ በመነሳት በሙብት ደረጃ ከሚገባቸው ቀንሰው በመቅረብ ብዙ የሞኮሩትን ሁሉ ራሳቸውን ኣስጠቅተው ሃገሪቱንና ህዝቡን ከመበደል ሌላ ፋይዳ ኣላስገኙም። ከዚህም ሁሉ በመማር ይመስላል ከምርጫ 97 በሃላ ኦነግ የወሰደው ኣቋም ኣይነተኛ ምሳሌ ነው። የኦነግም ኣቋም ኣወሳሰድ የጥቃት ሰለባ ሆነው ከቆዩት ሌሎች ተቃዋሚ ሃይሎች ጋር የበለጠ መተማመንን ሊፈጥር በመቻሉ የተቃዋሚዎች ጎራ እየተጠናከረ መጥቷል። በመሆኑም በሰራዊት ሃይል ብቻ በመተማመን በጉልበት ለመግዛት የቆረጠው ኢህኣደግ ከቀን ወደ ቀን እየባሰበት በሚታየው የሰራዊቱ መሸርሸር እንደተመኘው ፋታ ሊሰጠው ኣልቻለም።

ይህ በእነዲህ እንዳለ ድንበሩን ለማካለል የተሰየመው ኮምሽን በ11-19-06 የኣልጀርሱን ህጋዊነት የሌለውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ በ2002 ኮምሹኑ ራሱ ያስተላለፈውን ብይን በመንተራስ በ45 ካርታዎች ያዘጋጀውን ሁሉ ለተባበሩት መንግስታትና ለሁለቱም ባለጉዳይ መንግስታት (ኤርትራና ኢትዮጵያ) እንዲሁም ለሌሎች የሚመለከታቸው ኣካላት ይፋ ኣድርጌ እደመድማለሁ ማለቱን በሁላችንም ዘንድ ተደምጧል። ይሁን እንጂ ይህ ቧልት የኢትዮጵያ

ህዝብ ዛሬም እንደ ትላንት የማይቀበለው ለመሆኑ የሚመለከተው ሁሉ እንዲያውቀው ይገባል። ቀድሞም ቢሆን የኢትዮጵያ ህዝብ የአልጀርስ ውል የኢትዮጵያን ጥቅምና ሉአላዊነት አሳልፎ የሰጠ መሆኑን አበክሮ ያውቃል። አሁን በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስት እዚህ ግባ የማይባል ተልካሻ ምክንያት በመስጠት አገራችንን ካስወረረ በኋላ ጀግናው የሃገሪቱ ሰራዊት ደሙን አፍሶ ሉአላዊነታችንን በማስከበሩ ሂደት ላይ እያለ ባእድ መጥቶ ካልተደራደረልኝ ሙቼ እገኛለሁ በሚል ፊሊጥ የመለስ መንግሰት ከህዝብ በስተጀርባ የዶለተው ደባ መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ መልሶ መላልሶ ለተባበሩት መንግስታትና ለሌሎች የሚመለከታቸው ሁሉ ባለማቋረጥ አቤት ማለቱን አይዘነጋም። እንኳን ዘንቦብሽ ድሮውም ጤዛ ነሽ እንዲሉ አሁንማ ማለትም ከጎንበት 97 ዓ/ም በኋላ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሰት ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች በተገኙበት የህዝብን ይሁንታ የተነፈገው ለመሆኑ የአደባባይ ሚሰጥር ነው። በመሆኑም አገራችንን የሚመለከቱ ማናቸውም የመወያያ ነጥቦችም ይሁኑ ውሎች ስልጣን ላይ በተቀመጠው መንግስት እስከተደረጉ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብን የማይመለከቱና የማይደግፋቸው ለመሆናቸው በሁሉም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና ፍትህ አራማጅ ሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ተቆርቋሪ አገር ወዳድ ዜጎች በአስፈላጊው ወቅትና ቦታ ሊገለጽ እንደሚገባው ነው መጠቆም የምንወደው።

በተለይም ከጉንበት 7 1997 በኋላ በስልጣን ላይ ያለው መንግሰት ምንም አይነት ውክልና የሌለው መሆኑን ለዓለም በመታወቁ፤ ይህንን ግዙፍና ፀሃይ የሞቀ መረጃ በመጠቀም ማንኛውም ኢትዮጵያን የሚመለከት ነገር ሁሉ ህወሓት/ኢህአዴግ ተደራዳሪ ሊሆን እንደማይችል ለሚመለከታቸው ሁሉ በተደጋጋሚ ማስታወቅና ማስረዳት እንደሚጠበቅብን ነው የሚታየን። የኢትዮጵያ መከላከያ ሃይልም ከሁሉም በላይ ደሙን ያፈሰሰለት ጉዳይ ነውና አሁንም ባአመራር ላይ ተቀምጠው በሃገራችንና በህባችን ላይ ለሚሸርቡና ለሚቀልዱት ተባባሪ እንደማይሆን እምነታችን የላቀ ነው።

ፍትህ የሰፈነባት ኢትዮጵያ በህዝቧ ተጋድሎ እውን ይሆናል።

ጋሻ ለኢትዮጵያውያን

ታህሳስ 2006